**የተከበሩ አቶ ይርሳው ታምሬ!**

**የአማራ ብሔራዊ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባኤ!**

**የተከበራችሁ የም/ቤት አባላት!**

**ጥሪ የተደረገላችሁ እንግዶች!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

1. በአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀፅ 116 (2) እና የዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደገና ማቋቋሚያ፤ ማደራጃና ስልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 እና አንቀፅ 10(2) ለመ/ቤቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የተከናወኑ ተግባራትን የሚገልፅ ዓመታዊ አጭር ሪፖርት ዋና ኦዲተሩ ለተከበረው ም/ቤት እንደሚያቀርብ የተደነገገ በመሆኑ ይህን ሪፖርት አቀርባለሁ፡፡
2. በዚህ አጭር ሪፖርት የመ/ቤታችን የ2009 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፣ መ/ቤታችን ያከናወነው የ2007 በጀት ዓመት የክልሉን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ እና የ268 መ/ቤቶች የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሪፖርት በቀደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

**የ2009 በጀት ዓመት የ11 ወራት የዕቅድ አፈፃፀም፤**

**የኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አፈፃፀም**

3. በ5ቱ የአቅም ግንባታ ስትራቴጅዎች ማለትም በአመለካከት፣ በክህሎት፣ በአሰራር፣ በአደረጃጀትና በግብዓት የማብቃትና የልማት አቅሞችን ወደ ተቀራረበ የመፈፀም አቅም የማብቃት ጉዳይ ነው፡፡ ከኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ አንፃር በ2009 በጀት ዓመት የአቅም ግንባታ ስትራቴጅዎችን አፈፃፀም 75% በማድረስ፣ የግምባር ቀደም ሰራተኞችን ቁጥር 50% በማድረስ፣ ስራን በተደራጀ መንገድና በለውጥ ፕሮግራሞች አግባብ በመፈፀም ጠንካራ የኦዲት ልማት ሰራዊት ለመገንባት ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ ከዚህ አንፃር የመ/ቤታችን ፈፃሚዎች በ4 የልማት ቡድኖች እና በ72 የ1ለ5 አደረጃጀቶች ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግ ተችሏል፡፡

   አደረጃጀቶች በየቀኑ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ፣በየ2 ሳምንቱ በተመረጠ ርዕሰ-ጉዳይ መማማርና በቃለ-ጉባዔ የተደገፈ ውይይትና የስራ ላይ ግምገማ በየሳምንቱ በማድረግ፣በየጊዜውና በየደረጃው ግብረ-መልስ እየተሰጠ ለመምራት ጥረት ተደርጓል፡፡ የተቀራረበና የተለወጠ አመለካከት ለማምጣት የተለያዩ መድረኮችን በመፍጠር ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡

ለአብነትም-በ2008 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃጸም ግምገማና የ2009 በጀት ዓመት ዕቅድ ትውውቅ መድረክ፣ የነጥብ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ (JEG) በተመለከተ የተዘጋጀ መድረክ፣ የ6 ወራት አፈጻጸምና የጥልቅ ተሃድሶ ግምገማ ሂስ ግለሂስ መድረኮች፣በኦዲት ምንነት፣ አስፈላጊነትና አዘጋገብ ዙሪያ ለብዙሃን መገናኛ ድርጅት ባለሙያዎች (ጋዜጠኞች)፣በየደረጃው ላሉ የፍትህ አካላት፣ለማህበራት

ኦዲተሮች የተካሄዱ ሲሆን፤ለመ/ቤቱ ሰራተኞች (ኦዲተሮች)በተለያዩ ጊዜያት የተዘጋጁ የሙያ ስልጠናዎች ማካሄድና ተግባራትን በስታንዳርድ መሰረት የመፈጸም ብቃትንና ስነምግባር የተላበሰ አገልግሎት አሠጣትን በሚጠናክሩ ርዕሶች የተሰጡ መድረኮች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በዚህ ደረጃም በልማት ቡድንና መ/ቤት ደረጃ የተካሄዱ መድረኮች፤የተደረጉ ግምገማዎችና ውይይቶች ግልጽነትና የአመለካከት መቀራረብ እንድንፈጥርና የተገኙ ግብዓቶችና ክህሎቶችም ለዕቅዶቻችን ማሳካት አግዘውናል፡፡

4. ከመልካም አስተዳደር ስራዎች አንፃር በ2009 በጀት ዓመት ዕቅዳችን በርካታ ተግባራትን ለማከናዎን ማለትም የሪፎርም ስራዎችን አፈፃፀም አጠናክሮ ከማስቀጠል አጠቃላይ ዕይታ በመነሳት የህዝብ ከፍተኛ ጥቅም ያለባቸውን የከተሞች ልማት ዕድገት ፈንድ ተጠቃሚ ከተሞች ኦዲትንና የምዕተ-ዓመቱ ቀጣይነት ዕድገት በጀትን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል፤ የልዩ ኦዲት ስራ አመራርን መከታተያ መመሪያ በማሻሻል፤ ከዚህ ቀደም በተከታታይ በቅሬታ ለሚነሱ የኦዲት ስራዎች የአፈታት አቅጣጫ በማስቀመጥ፤ቅሬታዎችን ፈጥኖ ምላሽ መስጠት የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት የተሰሩ ጅምር ስራዎች በአበረታችነት የታዩ ናቸው፡፡

5. በኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ ሂደታችን ከዚህ በላይ የተመላከቱ ውጤቶች የመገኘቸውን ያክል ውስንነቶችና ትኩረት አግኝተው ሊቀረፉ የሚገባቸው ጉዳዮችም አሉ፡፡ በ11 ወሩ ግምባር ቀደሞችን ለማፍራት በተያዘው ዕቅድ መሰረት በምስራቅ አማራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት 21 ግምባር ቀደሞች፤ በዋናው መ/ቤት ደግሞ 65 በድምሩ 86 ግምባር ቀደሞች ቢለዩም ከዕቅዳችን አንፃር ግን በርካታ የሚቀሩን ስራዎች አሉ፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ውይይቶች የሚቆራረጡበት ሁኔታ (በተለይም በመስክ ኦዲተሮች)፤ የሪፎርም ስራዎችን በተከታታይነት በመተግበር ተገቢውን ትምህርት በመቅሰም የክህሎት ሽግግር አጋዥ መሳሪያዎች በማድረግ በኩል ውስንነቶች ይታያሉ፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ጊዚያት በዚህ ሪፖርት በጉልህነት የተለዩ ውስንነቶች ትኩረት አግኝተው ሊቀረፉ ይገባል፡፡

6. የውስጥና የውጭ ደንበኞች አገልግሎት አሰጣጣችን በየ6 ወሩ መረጃ በመሰብሰብ ከደንበኞች በአማካኝ 86% እርካታ እንዳለ የታየ ሲሆን ይህም በዓመቱ በዕቅድ ከተያዘው 91% አኳያ ሲታይ የዕቅድ አፈፃፀሙ 94% ነው፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ እርካታ መጠይቅ በማዘጋጀትና በኦዲት መውጫ ስብሰባ ወቅት ኦዲት አስዳራጊዎች በጽሁፍ በሚሰጧቸው አስተያየቶች መሰረት በጥንካሬ የተገለጹት በኦዲተሮች እየተሰጠ ያለው ድጋፍ በየጊዜው ያለባቸውን ክፍተት እየሞሉና ድክመታቸውን በማሳየት ትልቅ እገዛ እያደረገ መሆኑን፣ የኦዲት ስራው ማስረጃን መሠረት በማድረግ የሚቀርብ በመሆኑ ለሚዛናዊ ውሳኔና ለግልጽነትና ተጠያቂነት መጠናከር እያገዘ መሆኑን በተለይም በወቅታዊ አለመረጋጋት ሳይደናቀፍ የኦዲት ስራው መቀጠሉ፤ የኦዲት ስራው በየ6 ወሩ ተከፋፍሎ (በኢንትሪም

ኦዲት ስልት)መሰራቱ ያለውን የሚታዩ ስህተቶችን በወቅቱ ለማስተካከል ስለሚረዳ በዚሁ እንዲቀጥል መለካም ነው የሚሉ ገንቢ አስተያየቶች ናቸው፡፡

በውስንነት ደንበኞች የሰጧቸው አስተያየቶች ሲታዩ ባለሙያዎች ኦዲት ተደራጊዎችን በትህትናና በትዕግስት በማስተናገድ በኩል አልፎ አልፎ ውስንነት መታየቱ፣ በስራቸው ወቅት ስህተት ፈላጊነት መታየቱ፣ በየአመቱ የኦዲት አገልግሎት የማያገኙ ተቋማት መኖር፣ አልፎ አልፎ የኦዲት ጥራት ችግር ማጋጠሙ፣ በህብረተሰቡ ዘንድ የፈጠርነው የሙያው ግንዛቤ ገና ውስንነት ያለበት መሆኑ የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

7. የውጤት ተኮር ሥርዓት ከሪፎርም ፕሮግራሞች መካከል ትኩረት ተሰጥቶት በመተግበር ላይ ከመሆኑም ባሻገር አጠቃላይ ውጤቱም ከሌሎች የሪፎርም ስራዎች ጋር ተዳምሮ የመፈጸም አቅሙ የተሻለና መልካም አስተዳደርን ያሰፈነ ተቋማዊ ሁኔታን ማረጋገጥ የሚጠይቅ ነው፡፡ በተለይም ኦዲት በአጠቃላይ የመንግስት አሰራር ግልፀኝነትን የተላበሰና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን የሚያበረክተው አስተዋፅኦ የጎላ በመሆኑ በዚሁ አግባብ መፈተሽ ይኖርበታል፡፡

በ2009 በጀት ዓመት የ1ኛው ግማሽ ዓመት ውጤት ከተሞላላቸው 265 መካከል 64(24%) (ወ 54፣ሴ 10)ሠራተኞች ከፍተኛ ያገኙ ሲሆን ቀሪዎቹ 201 (76%) (ወ 149፣ሴ 52) ሰራተኞች የሚሆኑት ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ የተፈረጁ ናቸው፡፡

ከውጤት ተኮር ስርዓት ጋር በተያያዘ ያሉብን ውስንነቶች፣ የባለሙያ ምዘናው ሳይቆራረጥ በየወሩ አለማካሄድ፣የምዘና መረጃ አያያዙ ውስንነት ያለበት መሆንና በትግልና በመረጃ ላይ ተመስርቶ ተገቢውን ደረጃ አለመመዘን የታዩ ውስንነቶች ናቸው፡፡ውጤቱን ተከትሎ ወቅታዊ ግብረ-መልስ የመስጠት ችግርም የሚታይ በመሆኑ ከዚህ በመነሳት ለ2ኛው የ6 ወራት ውጤት ተኮር ስርዓት ከችግሮች በሚያወጣ መንገድ ውል ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

**የኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራዎች አፈፃፀም**

8. የኦዲት ኮሚዩኒኬሽን ስራችን በዋናነት የፋይናንስ ግልፀኝነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን በሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረቱን አድርጎ በሐገራዊ፣ ክልላዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ማህበረሰብ ግንዛቤ መፍጠርና የተቀራረበ የአመለካከት አንድነት መገንባት ታሳቢ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ በዚህም ለፍትህ አካላትና ለብዙሃን ማህበራት የግንዛቤ መፍጠሪያ የንቅናቄ መድረክ ማዘጋጀት፣ የህትመት ስራዎችን ማሳተምና ተደራሽ ማድረግ የዕቅዳችን አካል የነበሩ ሲሆን በ11 ወሩ ውስጥ መድረክ መፍጠርና ተደራሽነትን ለማሳካት ጥረት ተደርጓል፡፡ሐገራዊና ክልላዊ ሁኔቶች መሠረት ያደረገ በፖሊሲና ስትራቴጅዎች ብሎም በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ በመ/ቤት ደረጃ መድረኮች በማዘጋጀትና ግንዛቤ በመፍጠር ጥሩ መግባባት የተደረሰባቸው መድረኮች ነበሩ፡፡ ኦዲት ሪቪው ዓመታዊ የሙያና መጽሔትና ዜና ኦዲት መጽሔት ህትመቶች ተከናውነዋል፡፡

**የኦዲት ሥራ ዕቅድ አፈፃፀም፤**

**የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት አፈፃፀም**

9. በ2009 በጀት ዓመት በፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ሽፋን ቅድሚያ ተሰጥቶ ኦዲት መደረግ ከሚገባቸው 442 መ/ቤቶች አንፃር 65% ለማድረስ እና በበጀት ዓመቱ 288 መ/ቤቶችን ኦዲት ለማከናወን ዕቅድ ተይዞ በኦዲት መሸፈን የተቻለው የ268 መ/ቤቶችን በመሆኑ አፈፃፀሙ ከዓመቱ ዕቅድ አንፃር 93.05% ሲሆን የኦዲት ሽፋናችን ከጠቅላላ ቅድሚያ ኦዲት ሽፋን እንዲያገኙ ከተለዩት 442 መ/ቤች ጋር ሲነጻጸር 60.63% አድርሶታል፡፡ይህም ለዓመቱ የተያዘውን እቅድ ማሳካት እንደሚቻል መገመት ያስችላል፡፡

10. ሽፋን ከበጀት አንፃር እስከ 70% የወጪ በጀት እና እስከ 35% የገቢ በጀት ሽፋን ለማድረስ ታቅዶ ለክልሉ የ2008 በጀት ዓመት የተፈቀደውን አጠቃላይ በጀት ብር 27.297 ቢሊዮን መነሻ በመያዝ በኦዲት የተሸፈኑ መ/ቤቶች አጠቃላይ በጀት ብር 23.498 ቢሊዮን የኦዲት ሽፋን ያገኘ በመሆኑ አፈፃፀሙ 86.08% ደርሷል፡፡ ይህም በቢሮ ደረጃ ከፍተኛ በጀት የያዙና የዘላቂ ልማት በጀት ፈጻሚ ተቋማት ሂሳብ ኦዲት ሽፋን በመሰጠቱ ምክንያት ከዕቅድ በላይ መሸፈኑን ሲያሳይ ሁኔታው ከላይ በቁጥር በተመለከተው ሽፋን ላይ የራሱ ጫና ነበረው፡፡

የገቢ ኦዲት ሽፋንን በሚመለከት ክልሉ በራሱ አቅም ለመሰብሰብ የያዘው አጠቃላይ ገቢ ብር 7.453 ቢሊዮን በመሆኑ ኦዲት የተደረጉት ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች ሽፋን ያገኘው ብር 1.461 ቢሊዮን በመሆኑ ሽፋኑ 20% የተጠጋ ነው፡፡ ይህ አፈፃፀም ዝቅ ያለ ሲሆን በአዲስ መልክ በተጀመረው ገቢን ከወጪ ሂሳብ ጋር ጎን ለጎን አጣምሮ ኦዲት የማድረግ ስትራቴጂ በቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን በኩል የገቢ ሂሳብ ኦዲት በከፊል ባለመሰራቱ ያጋጠመ ችግር ነው፡፡ በ2009 በጀት ዓመት አሠራሩ ተስተካክሎ በመሠራት ላይ ስለሆነ ሽፋኑ ከፍ የሚል ይሆናል፡፡

**የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት በተመለከተ፤**

11. መ/ቤታችን በየዓመቱ ተዘግቶ የሚቀርብለትን የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት እያደረገ አስተያየት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡በዚህም መሠረት የ2007 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ኦዲት ተጠናቆ ‹‹ከዚህ በስተቀር›› የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን በግኝቶቹ ላይም የማስተካከያ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ት/ቢሮ በግብረ መልሱ ገልጿል፡፡ ዋና ዋና ግኝቶችም በዚህ ሪፖርት ቀርበዋል፡፡ በሌላ በኩል የ2008 በጀት ዓመት የተጠቃለለው ፈንድ ሂሳብ ተዘግቶ ስለደረሰን የኦዲት ስራው ከ75% በላይ ተከናውኖ ቀሪ የመስክ ስራው በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡

**የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት አፈፃፀም፤**

12. ከክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት አንፃር በ2009 በጀት ዓመት ሒደቱን ራሱን አስችሎ ማደራጀት፣ በ2007 እና 2008 በጀት ዓመታት እየተሰሩ የዞሩ 14 ስራዎችን ማጠናቀቅና አዲስ የሚጀመሩ

መ/ቤቶችን በመደበኛ ኦዲትና ሌሎች 6 መ/ቤቶችን የክትትል ኦዲት ስራዎችን ለመስራት ዕቅድ ተይዞ ነበር፡፡ የክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ራሱን ችሎ በዳይሬክቶሬት ደረጃ የተደራጀና 10 የኦዲት ቡድኖችን ይዞ ዓለም አቀፍ ደረጃውን (ስታንዳርድን) እንዲያሟላ ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሠረትም በ2008/9 የኦዲት ስራቸው ተጠናቆ ሪፖርት ወጪ የሆኑባቸውን በጠቅላላው 16 መ/ቤቶችን የመደበኛ ክዋኔና የክዋኔ ክትትል ኦዲት ስራ ውጤቶች በየካቲት ወር/2009 ላይ ለተካሄደው የምክር ቤት ጉባዔ ያቀረብን ሲሆን በጉባዔውም እንዲመከርባቸው፤ አቅጣጫ እንዲሰጥባቸውና እንዲጸድቁ ተደርጓል፡፡

በ2009 በጀት ዓመት ሊሰሩ የታቀዱት 6 የክዋኔ ክትትል ኦዲት ስራዎች ተጠናቀው ሪፖርታቸው ወጪ ተደርጎ ለሚመለከታቸው ተላልፏል፡፡ ሌሎች የታቀዱ 8 የመደበኛ ክዋኔ ኦዲት ስራዎች በመስክ ላይ እየተከናወኑ ሲሆን በአጠቃላይ በ11 ወሩ የ10.6 መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ እቅድ ተይዞ በአንፃራዊ ስሌት የ9.69 መ/ቤቶችን ሂሣብ ኦዲት በማድረግ የእቅዱን 91.4% ለማከናወን ተችሏል፡፡

**የኦዲት ስልጠና ክትትልና የሙያ ብቃት ፈቃድ አሰጣጥ አፈፃፀም፤**

13. መ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 186/2003 አንቀፅ 6 (2) (ሀ) መሰረት የመንግስት መ/ቤቶችንና የልማት ድርጅቶችን በውክልና ኦዲት እንደሚያስደርግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሂሳባቸውን በግል ኦዲተሮች ላስመረመሩና በማስመርመር ላይ ለሚገኙ የክልሉ መንግስት የልማት ተቋማት፤ የየከተሞች የውሃና ፍስሽ አገልግሎት ጽ/ቤቶችና ከከተማ አስተዳደር በታች ያላቸውን ማዘጋጃ ቤቶች በቁር 39 በሚሆኑት ላይ የክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰተርቷል፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር በተያያዘ ለግል ሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች ፈቃድ መስጠትና የስራ ክትትል ተግባርን በተመለከተ በ11 ወሩ መስፈርቱን ላሟሉና በሙያው ለቀረበ ፈተና የማለፊያ ውጤት ላገኙ በድምሩ ለ158 (ወ 139፤ሴ19) የሒሳብ ሙያ ፈቃድ ጠያቂዎችና ለ29 (ወንዶች) የኦዲተር ሙያ ፈቃድ ጥያቄ ላቀረቡ ባለሙያዎች የሙያ ፈቃድ ተሰቷል፡፡

ስልጠናን በሚመለከት ኦዲተሮች በቅድመ ስራና የስራ ላይ ሠልጣኞች ደረጃ ተለይተው ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የአቅም ግንባታ ስራ እየተካሄደ ቆይቷል፡፡ከዚህም መካከል፤ ለጀማሪ ኦዲተሮች በኦዲት ሙያ፣ በመንግስት ሂሳብ አያያዝ፣ በኦዲት ሙያ ስነ-ምግባርና በመንግስት ፖሊሲዎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በድምሩ ለ27 (18 ወንድና 9 ሴት) ኦዲተሮች፤ ለክዋኔና አካባቢ ጥበቃ ኦዲት ማናጀሮችና ፈጻሚ ኦዲተሮች በድምሩ ለ38 (35 ወንድና 3 ሴት) ባለሙያዎች፤ ለፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት ባለሙያዎች በኦዲት አሰራር ዘዴና ሂደት በሙያው የጋራ ወጥ አሰራርን ስለመከተልና በኦዲት ወቅት ባጋጠሙ የአሰራር ችግሮች ላይ በድምሩ ለ202(156 ወንድና 46 ሴት) ኦዲተሮች ሙያዊ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤቶች ስራ አስኪያጆች ፣አስተባባሪዎች፣ የውስጥ ኦዲተሮችና

አማራሮች በ2 ዙር በአጠቃላይ በድምሩ ለ365 (305 ወንድና 60 ሴት) የሙያ ማስገንዘቢያ ስልጠና ተሰጧል፡፡ ይህም በየጽቤቶቹ ያለውን የሃብት አስተዳደርና አጠቃቀመ በማሻሻል አገልግሎት አሰታትን ለማሻሻል እንዲችሉና ለግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓት መጎልበት ጉልህ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

እነዚህ ሁሉ የአቅም ግንባታ ስራዎች ባለሙያዎች አለም ዓቀፍ የኦዲት አሠራርና የስነ-ምግባር ደረጃዎችን ጠብቀው ኦዲቱን እንዲሰሩና ውጤታማነታቸው እንዲያድግ ብሎም ክህሎታቸውን ለአዳዲስ ባለሙያዎች በማስተላልፍ የሙያ አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ ያደርጋል፡፡

**የሰው ሃይል መዋቅርና የስምሪት መረጃ፤**

14. መ/ቤቱ የደሴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሠራተኞችን ጨምሮ 334 የሰው ኃይል የሚይዝ ድርጅታዊ መዋቅር ያለው ሲሆን ግንቦት 30/2009 ላይ ያለው የሰው ኃይል ብዛት 293 (87.7%) ሲሆን ከዚህ ውስጥ 213 (72.6%)አላማ ፈፃሚ እና 80(27.4%) ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ናቸው፡፡ በትምህርት ዝግጅት ዲግሪና ከዛ በላይ ያላቸው ድምር 237 (79%) (ሴ 44 ፤ወ 193) ናቸው፡፡

 በመ/ቤቱ በስራ ላይ ካሉት 293 ሠራተኞች መካከል 216 (73.7%) ወንዶች፣ 77(26.3%) ሴቶች ናቸው፡፡ ከኃላፊነት አንፃር የሴቶች ተሳትፎ ሲታይ 6 ባለሙያዎች ከዳይሬክተር እስከ ኬዝ ቲም አስተባባሪ በመካከለኛ የአመራር ሃላፊነት ደረጃ የያዙ ይገኙበታል፡፡ከዓላማ ፈፃሚዎች መካከል 4 ተሿሚዎች ናቸው፡፡

 ከዚህ ውስጥ በ2009 በጀት ዓመት የ11 ወር በተለያዩ ስምሪቶች የተሟላው 19 ወንድና 9 ሴት በድምሩ 28 በአዲስ ቅጥር የተሟላ ሲሆን ተመሳሳይ ወቅት 42 ሰራተኞች(2 በጡረታ) በራሳቸው ፈቃድ መ/ቤቱን ለቀዋል፡፡

 ከረጅም ጊዜ ትምህርት አንጻር ለ2009 በጀት ዓመት በሙያው በ2ኛ ዲግሪ በክረምት ፕሮግራም 10 ሰራተኞችን ለማስተማር ታቅዶ የነበረ ሲሆን 9 ትምህርቱን የጀመሩ ሲሆን ቀደም ሲል እየተማሩ የቆዩትን አካቶ በ2ኛ ዲግሪ ትምህረት ላይ የሚገኙ 13 (8 ወ፤5 ሴ) ሲሆኑ በተጨማሪም ከደረጃ 1-4 እና ዲኘሎማ ያላቸው ለዲግሪ የሚማሩትን ጨምሮ በአጠቃላይ በትምህርት ላይ ካሉት 24 (9 ሴ፣ 15 ወ) ሠራተኞች መካከል ናቸው፡፡

**የበጀት አፈፃፀምና አጠቃቀም**

15. በ2009 በጀት ዓመት ብር 16,213,944.00 ለደመወዝና ብር 17,508,764.00 ለመደበኛ ስራ ማስኬጃ እና ለካፒታል ብር 846,306.00 በድምሩ ብር 34,568,708.00 የተስተካከለ በጀት በመያዝ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርጓል፡፡ የ11 ወሩ በጀት አጠቃቀም ሲታይ ከመደበኛ በጀት ለደመወዝ ብር 13,821,556.44፣ ለስራ ማስኬጃ ብር 14,943,399.17 በድምሩ ብር 28,764,955.61 (ከዓመቱ በጀት 85.3%) ነው፡፡ የካፒታል በጀት ደግሞ የቅድሚያ ክፍያን አካቶ አፈጻጸሙ 575,000.00 (66.5%) ነው፡፡ የካፒታል በጀቱ አጠቃቀም ሲታይ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ለማጠናቀቅና ውል ይዞ ወደ ጥገና ስራው

ለመግባት የወሰደው ጊዜ ሰፊ በመሆኑ አፈጻጸሙ ውስንነት ይታይበታል፡፡

በሌላ በኩል የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ፕሮግራም (PBS-III) ከተመደበልን በጀት 97.7% እና ከከተሞች ድጋፍ ፕሮግራም (ULGDP-II) በጀት ላይም 87% ስራ ላይ ውሏል፡፡

በዚህ የበጀት አፈጻጸም ወቅት የተመደበውን በጀት በተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት መሠረት ለመምራት ጥረት የተደረገ ሲሆን በውስጥ ኦዲተሮቻችን አማካኝነት እየተመረመረ ለሪፖርቱ ግብረ-መልስ እየተሰጠ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ጭምር የተላከ ሲሆን የተስተዋሉ የክፍያ፤የምዝገባና ተያያዥ ግኝቶች ላይ ከስር ከስሩ የማሻሻያ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡

የግዥ አፈጻጸሙን በተመለከተ በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ በተያዘው የግዥ እቅድ መሠረት አብዛኛውን ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ በወቅቱ ለማከናወን ተችሏል፡፡ የመ/ቤቱ የንብረት አያያዝ በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውል እየተደረገ ሲሆን ለኦዲት ምቹ፤ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ሆኖ እንዲተገበር እየተደረገ ይገኛል፡፡

**የሴክተር ዘለል ተግባራት አፈፃፀም፤**

**የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ስራዎች**

16. የመ/ቤቱ ሠራተኞች ከየወሩ ደመወዛቸው እያዋጡ በሚያጠራቅሙት የጸረ ኤች.አይ.ቪ/አድስ ፈንድ ማህበር ቫይረሱ በደማቸው ያለባቸው ባልደረቦችና ማህበሩ ለሚያሳድጋቸው 2 ህጻናት ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡

    የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ተግባራትን አካቶ መስራት(ሜይንስትሪሚንግ) ዕቅድ ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው የላከ ሲሆን በቢሮ ውስጥ ሠራተኞች በየወሩ አንድ ጊዜ ስለቅድመ ጥንቃቄው፤ስለቫይረሱ ባህሪ፤ የመተላለፊያውና መከላከያ ዘዴዎቹ ውይይት እየተደረገና በየሩብ ዓመት ሪፖርት እየተዘጋጀ ለሚመለከተው በመተላለፍ ላይ ይገኛል፡፡

**ስርዓተ ፆታን አካቶ የመስራት እንቅስቃሴ፤**

17. ስለስርዓተ ጾታ ተገቢውን ግንዛቤ በመያዝ በሁሉም ስራ አካቶ በመስራትና ሪፖርቶችም በጾታ ተተንትነው የሚቀርቡበት ስርዓት ተዘርግቶ እየተፈጸመ ሲሆን በሴቶች ልዩ ማበረታቻ መመሪያ መሰረት በ11 ወሩ ከተፈፀመው 20 የቅጥር ስምሪት ላይ 6 ሴቶች በልዩ ማበረታቻው መሰረት የተቀጠሩ ናቸው፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

ቀጥሎ የ2007 በጀት ዓመት የክልሉ የተጠቃለለ ፈንድ (የትሬዠሪ) ሂሣብ ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶችን አቀርባለሁ፤

**ያልተሰበሰበ /ያልተወራረደ፤ያልተወገደ/ የተሰብሳቢ ሂሳብ**

18. በክልሉ ውስጥ በአጠቃላይ የሚገኘው የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 7,088,213,071.28 ሲሆን በዝርዝር ሲታይ ሂሳቡ በእድሜ ተተንትኖ ያልተያዘ በመሆኑ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየ ማረጋገጥና በ2006 በጀት ዓመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደ እንዲሁም በበጀት ዓመቱ የተጨመረውን ለይቶ አስተያየት ለመስጠት የማያስችል ሲሆን በ2006 በጀት አመት ከነበረው የተሰብሳቢ ሂሳብ ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በብር 1,239,829,214.19 /21.2%/ እድገት ያሳያል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ6 ቢሮዎች የተያዘው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት(MDG/ SDG) የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 2,239,203,951.57 /32%/ ሲሆን ይህም በ2006 በጀት ዓመት ከነበረው የMDG ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 1,568,744,083.68 ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በ43% የጨመረ መሆኑን ያሳያል፡፡
ስለሆነም እየተወሰደ ያለው እርምጃ አዝጋሚ በመሆኑ ሂሳቡ በዕድሜ ተተንትኖ እንዲሰራና መግለጫውን ለቢሮው እንዲያቀርቡ በማድረግ መወራረድ የሚችለውን ሂሳብ ማወራረድ እንዳለበትና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊሰበሰብ የማይችለውን ደግሞ ቀደም ሲል በወጣው የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 6/2004 አንቀፅ 14 ን/አ 1-5 መሰረት ከመዝገብ ሊሰረዝ እንደሚገባ በዝርዝር አስገንዝበናል፡፡

**ለሚመለከተው ያልተከፈለ የተከፋይ ሂሳብ**

19. በክልሉ ውስጥ በአጠቃላይ የሚገኘውን የተከፋይ ሂሳብ ብር 3,944,574,166.99 ሲሆን ይህ ሂሳብ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆየና በ2006 በጀት ዓመት ተይዞ ከነበረው የተከፋይ ሂሳብ ውስጥ ምን ያህሉ እንደተወራረደና በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተጨመረውን በመለየት አስተያየት ለመስጠት በሚያስችል መንገድ አልተያዘም፡፡ የ2007 በጀት አመት የተከፋይ ሂሳብ በ2006 በጀት አመት ከነበረው ጋር በጥቅል ሲነፃፀር በብር 591,620,360.69 /18%/ እድገት አሳይቷል፡፡ ከዚህ ውስጥ በ6 ቢሮዎች የተያዘው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ማስፈፀሚያ በጀት /MDG/ የተከፋይ ሂሳብ

ብር 407,027,747.37/13%/ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለሆነም የስራ ተቋራጮች የቅድሚ ክፍያ፣ የጡረታ ተከፋይ፣ ሌሎች የደመወዝ ተቀናናሾች፣ 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በገዥው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ለሚመለከታቸው ወቅቱን ጠብቆ ያለማስተላለፍ ምክንያት የተፈጠረ የተከፋይ ሲሆን ሂሳብ በእድሜ ተተንትኖ ሊያዝና በየወቅቱ መከፈል የሚችለውን ሂሳብ ለሚመለከታቸው ሊከፈልና ምክንያቱ ተጣርቶ ሊከፈል የማይችለው /ባለቤት የሌለው/ ሂሳብ ደግሞ ወደ ሀብትነት ተቀይሮ ስራ ላይ እንዲውል አሳስበናል፡፡

**የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ ሂሳብ፤**

20. በቢሮው የተጠቃለለው የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛን ያላቸው ለመሆኑ በናሙና የተመረጡ ሪፖርት አቅራቢዎች (በክልል ቢሮዎችና ወረዳዎች) የሂሳብ ሪፖርት ሲታይ የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ የመደበኛ በጀት ሂሳብ ላይ የባንክ ሂሳብ፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣ የተከፋይና የተጣራ ሃብት ሂሳብ በድምሩ ብር 8,016,823.08 ሲሆን የተፈጥሮ ሚዛኑን ያልጠበቀ ሂሳብ ስርዓቱን ያልተከተለ ምዝገባ ከመሆን ባለፈ ያልተገባ ተግባር ውጤት ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡

ስለሆነም ስለተዘጋጀው አመታዊ ሪፖርት ትክክለኛ መረጃ የማይሰጥና በተጣራ ሃብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚፈጥር በመሆኑ የሪፖርቱን ትክክለኛነት የተዛባና አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ምክንያቱን በማጣራት ተገቢው የማስተካካያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የሪፖርት አቅራቢ መ/ቤቶች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን ለቢሮው በሚያቀርቡበት ጊዜ ሁሉም ሂሳቦች መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆኑ እየተረጋገጠ ሊሆን እንደሚገባ አስገንዝበን ቢሮው በሰተው ግብረ መልስ በሁሉም ግንቶች ላይ የማስተካከያ እርምጅ ለመውሰድ በየደረጃው እየተደረገ ያሉትን ጥረቶች በመግለጽ በተለይም በተሰብሳቢና በተከፋይ ሂሳብ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት እየሠራ መሆኑን ገልጧል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**መ/ቤታችን ከጥር 2008 እስከ የካቲት 2009 ባለው ጊዜ ያከናወነውን የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲትና የልዩ ኦዲት ውጤት ዋና ዋና ግኝቶች እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡**

21. መ/ቤቱ በዚህ ሪፖርት ያካተተው የ268 መ/ቤቶች የ2008 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት ውጤት ነው፡፡ የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በአወቃቀር እርከን ሲታይ በክልል/ማእከል 73(27%)፣በዞን 11(4%)፤በከተማ አስተዳደሮች 41(15%) ቀሪዎች 143 (54%)፤ በወረዳ ደረጃ ያሉ ናቸው።

22. ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች፣ የሂሳብ መግለጫዎች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች የሠጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ከ3ኛ ወገን የተገኙ ብቃትና ተቀባይነት ያላቸው ማስረጃዎች ሥራ ላይ ውለዋል። የመ/ቤቶቹን ሂሳብ ኦዲት ማድረግ የመ/ቤታችን ኃላፊነት ሲሆን የሂሣብ መግለጫዎች የማዘጋጀት፣ ኦዲት የማስደረግና የሠሩበትን ሁኔታ የማስረዳት እንዲሁም በኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊነት ነው። ከኦዲት ስልት አንፃር ከ268 መ/ቤቶች ውስጥ 221(82.47%) በንሞና እንዲሁም 47(17.53%) መ/ቤቶች የልዩ ኦዲት ጥቆማ በመቅረቡ በዝርዝር ኦዲት የተደረጉ ናቸው፡፡

23. **የኦዲት አስተያየት** የ2008 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት ከተደረጉ 268 መ/ቤቶች መካከል የኦዲት አስተያየት የተሰጠባቸው 215 መ/ቤቶች ናቸው፡፡ ለ6 (2%) መ/ቤቶች ***"ንፁህ የኦዲት አስተያየት"*** ፤ለ203 (76%) መ/ቤቶች ***"ከዚህ በስተቀር"*** ፤ለ3 (1%) መ/ቤቶች **"አጥጋቢ አይደለም"**፤ለ3 (1%) መ/ቤቶች **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶአል፡፡ የኦዲት አስተያየቱ ከ2007 በጀት ዓመት የሂሳብ ኦዲት ጋር ሲነፃፀር የከዚህ በስተቀር አስተያየት ተቀራራቢ ሲሆን "ንፁህ የኦዲት አስተያየት" በ1 መ/ቤት እና "አጥጋቢ አይደለም" ደግሞ በአንፃሩ በ3 መ/ቤቶች ጨምሯል፤ **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** ደግሞ በአንፃሩ በ2 መ/ቤቶች ቀንሷል፡፡ ይህም ከ2006 የኦዲት አስተያየት ጋር ሲነጻጸር መሠረታዊ ለውጥ ባይሆንም መጠነኛ መሻሻሎች መኖራቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

24. የገንዘብ አያያዝና አስተዳደሩም ሆነ የዉስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱን መርምሮ ተዓማኒና በቂ የሂሳብ አያያዝና አስተዳደር መኖሩን ለማረጋገጥና የሙያ አስተያየት ለመስጠት ያላስቻሉ ጉልህና

መሰረታዊ ችግር የተገኘባቸው በመሆኑ **"አስተያየት መስጠት አልተቻለም"** የሚል የኦዲት አስተያየት የተሰጣቸው መ/ቤቶች፡-ሜጫ ወረዳ፣ታች ጋይንት ወረዳ እና ላይ ጋይንት ወረዳ ነጠላ ፋይናንስ ድጋፍ ሰጭ ማዕከላት ናቸው፡፡

መንግሥት የመደበላቸውን ሀብት /ገንዘብ/ በአግባቡና ህጉ በሚፈቅደው አሰራር መሠረት ስራ ላይ ያላዋሉ፤የማጭበርበር ተንኮል የተፈፀመባቸው፣ጉልህና መሠረታዊ ግኝቶችና የአሰራር ችግሮች የተስተዋሉባቸው በመሆኑ **"አጥጋቢ አይደለም"** የሚል አስተያየት የተሰጠባቸው መ/ቤቶች □□ሞ ወልዲያ ሆስፒታል፣እንሳሮ ወረዳ እና ሸዋሮቢት ከተማ አስተ/ፋይናንስ ድ/ሰጭ ማዕከላት ናቸው፡፡

### የኦዲት ሪፖርቶች ምላሽ አሰጣጥ

25. በመደበኛ ኦዲት ከተደረጉ 221 መ/ቤቶች መልስ ያልሰጡት 22(9.95%) መ/ቤቶች ናቸው፡፡ የዚህ ዓመት መልስ አሰጣጥ ካለፈዉ በጀት ዓመት ጋር ሲነፃፀር መሰረታዊ ለውጥ የታየበት ቢሆንም የመሻሻሉ ምክንያት መ/ቤታችን ተደጋጋሚ ቅስቀሳና ግፊት በማድረጉ ስለሆነ ለወደፊቱ የተዘረጋውን የአሰራር ስርዓት ተከትለው ምላሽ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ ኦዲት ተደራጊ ተቋማት ላይ በአዋጁ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ ምላሽ ያልሰጡ መ/ቤቶችም፤

- ሰቆጣ ማረሚያ ቤት፣ ሰሜን አቸፈር ወረዳ ከለላ ወረዳ
- በጎምድር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ፣ መሀል ሳይንት ወረዳ፣ ስናን ወረዳ
- ደብረ ታቦር ከተማ አስ/ገቢዎች ጽ/ቤት፣ መተማ ወረዳ፣ ቡግና ወረዳ
- ቦረና ወረዳ፣ ወረባቦ ወረዳ፣ ወረኢሉ ወረዳ፣
- መራ ቤቴ ወረዳ፣ መሀል ሜዳ ወረዳ ታች ጋይት ወረዳ፣
- ሊቦ ከምከም ወረዳ ፣ አንከሻ ጓጉሳ ወረዳ፣ ዳንግላ ወረዳ፣
- ዳህና ወረዳ፤ ዝቋላ ወረዳ፤ ወንበርማ ወረዳ እና መቅደላ ወረዳ ነ/ፋድ/ሰ/ማዕከል ናቸው፡፡

### የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ውጤት

### የጥሬ ገንዘብ ጉድለትና ብል□

26. የ2008 በጀት ዓመት ሒሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች በድምሩ ብር 667,269.82 ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 414,760.32 ከቀትሞ ገ/ያገሮች የተገኘ ነው፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (ሰኔ 30) በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበትና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ ጥሬ ገንዘብ ሲነጻጸር በ15 መ/ቤት ብር 4,735,882.41 የሌጀር ከወጪ ቀሪ በመብለጥ (የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በማነስ) እና በ2 መ/ቤት 1,352,042.31 በማነስ

ተስተውሏል፡፡

ከጥሬ ገንዘብ ጉድለቱ ብር 25,441.67 የተተካ ሲሆን ብር 218,953.72 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ እንዲሁም ማስረጃ በማጣራት ሂደት ያለ መሆኑ ከፍትህ ቢሮ የተገለፀልን ሲሆን በቀሪው ጉድለት ላይ ግን ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ ግብረ-መልስ ባለመምጣቱ የተወሰደውን እርምጃ ማወቅ አልተቻለም፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች**

27. 64 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡ (ዝርዝራቸው በዋናው ዘገባ ሪፖርት ተመልክቷል፡)

**የገቢ ሒሳብ ኦዲት ውጤት**

***የማጭበርበር ወንጀል የተፈፀመበት የገቢ ሂሳብ እና ዘዴዎች፣***

28. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ5 መ/ቤቶች ብር 3,178,432.91 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡ማጭበርበሩ የተፈጸመባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ስማዳ ወረዳ ገቢዎች ጽ/ቤት ብር 2,977,097.94 ከጥር 1/2003 ዓ.ም እስከ መስከረም 30/2009 ዓ.ም የተሰበሰበዉ ገቢ በትክክል ለወረዳዉ ባንክ አካውንት ገቢ መደረግ ሲገባው ፈሰስ ሳይደረግ በገንዘብ ያዥ ተሰብስቦ ለግል ጥቅም የዋለ ገቢ፣
- ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 115,913.53 በድርቅ ተጠቂ ለሆኑ ቀበሌዎች የመንገድ ቆረጣ ስራ ማሽነሪ ክራይ ክፍያ ሲፈፀም ተቋራጩ በገቢዎች ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስቡ ከተፈቀደው ደረሰኝ ውጭ በተጭበረበረ መንገድ ህጋዊ ያልሆነ ደረሰኝ አሳትመው በመሰብሰብ ለግል ጥቅም የዋለ ገቢ፣
- እንፍራንዝ ከተማ ንዑስ መዘጋጃ ቤት ብር 41,705.78 የገቢ ደረሰኝ በማበላለጥ፣ በመሰረዝ፣ ኦዲት የተደረገ ሰነድ በፍሉድ በማስተካከል የስመንብረት ዝውውር በማከናወንና የቀበሌን ባህር ዛፍ በመሸጥ ለግል ጥቅም የዋለ፣
- ተሁለደሬ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 40,250.66 ለገጠር ቀበሌዎች የመንገድ ተደራሽነት ስራ ለተሰራበት ማሽነሪ ክራይ ክፍያ ሲፈፀም ተቋራጩ በገቢዎች ጽ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲሰበስቡ ከተፈቀደው ደረሰኝ ውጭ በተጭበረበረ መንገድ ህጋዊ ያልሆነ ደረሰኝ አሳትሞ በመሰብሰብ ለግል ጥቅም የዋለ ገቢ የሚሉት ከፍተኛውን መጠን የያዙ ናቸው፡፡

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት አካላት የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ

ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 2,977,097.74 በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ውሳኔው እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

**ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ያለተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤**

29. የተጨማሪ እሴት ታክስን አስመልክቶ በወጡ ደንብና መመሪያዎች መሠረት ማንኛውም በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት ደረጃ የሚገኝ ድርጅት በከፋይነት ተመዝግቦ አገልግሎት ለሚሰጠው አካል ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ ያለበትና ግዥ የሚፈጽሙ አካላትም ማስረጃ እንዲቀርብላቸው የማድረግ ሃላፊነት የተጣለባቸው ቢሆንም በ9 መ/ቤቶች ብር 2,916,894.29 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈፀሙ መ/ቤቶች ዝርዝር፡-

- **ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ብር** 1,759,457.54 የስታዲዮም ግንባታ ለተቋራጩ ክፍያ ሲፈፀም፤
- **አስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ቢሮ ብር** 407,614.41 ከብረታ ብረትና ኢንጅነሪን ኮርፖሬሽን መሳሪያ ግዥ ሲፈፀም፤
- **ወንበርማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 297,768.50፤በፍርድ ቤት በተሰጠ ትዕዛዝ መሰረት ለህንፃ ስራ ተቋራጭ ማህበራት እና በከፍተኛ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ለአብክመ ቤቶች ልማትና ግንባታ አ/ማ ክፍያ ሲፈፀም፣
- **አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 180,593.33 በወረዳው የትምህርት ቤት እና የጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ሲፈፀም፤
- **ቢብኝ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 142,159.19 የአስተዳደር ቢሮ እና ቤተ-መጽሀፍት ለተሰራበት ክፍያ ለተቋራጭ ሲፈፀም፤
- **ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 48,882.49 ከወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ጤና ኬላ የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ሲፈፀም፣ ለአስተዳደር ቢሮ ግንባታ ክፍያ ሲፈጸም፤
- **መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 48,199.03 የወረዳው ሴክተር መ/ቤቶች ቢሮ ግንባታ ለተከናወነበት ክፍያ ሲፈፀም የሚሉት ከብር 40,000.00 በላይ ከአቅራቢው የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ የፈጸሙ መ/ቤቶች ናቸው፡፡

በመሆኑም ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ያለተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ የተሰበሰበና ለግል ጥቅም የዋለ በመሆኑ ያለደረሰኝ ታክሱን የወሰዱ አካላት ለገቢ ሰብሳቢው አካል ገቢ አድርገው ማስረጃ እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት ታክሱን ለመመለስ ፈቃደኛ ካልሆኑ በህግ አግባብ ክስ በመመስረት ከተጠቃሚው ያለደረሰኝ የተወሰደው የተጨማሪ እሴት ታክስ ለመንግስት ገቢ መደረግ

እንዳለበት በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰም፡፡

**ያልተሰበሰበ (በውዝፍ) የሚገኝ ገቢ፤**

30. የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ 268 መ/ቤቶች ውስጥ በ107 መ/ቤቶች ብር **30,395,650.08** ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ከፍተኛ ያልተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ ከሚታይባቸው ዞኖች መካከል ምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር ብር 8,089,715.65(26.6%)፣ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ብር 5,223,594.88 (17.18%) እና ደ/ጎንደር ዞን አስተዳደር ብር 4,441,302.75(14.61%) ከፍተኛውን ትርሻ ይይዛሉ፡፡ ያልተሰበሰበ ገቢ ተብሎ ከተያዘው ዉስጥ ብር 27,308.00(0.09%) ብቻ ስለመሰብሰቡ በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ቀሪው ብር 30,368,342.08 የተሰበሰበ ስለመሆኑ ይህ ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ሰኔ 23/2009 ዓ/ም ድረስ መልስ ያልተሰጠበት ነው፡፡

**ያልተሰበሰበ 2% የንግድ ትርፍ ግብር፤**

31. በገቢ ግብር አዋጅና ደንብ እንደተመለከተው ከተወሰነ መጠን በላይ የሆነ የእቃና አገልግሎት ክፍያ ሲፈጸም ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ተቀንሶ መሰሠብሰብ የሚገባው 2% የንግድ ስራ ትርፍ ግብር ከ19 መ/ቤቶች በድምሩ ብር **1,362,800.12** ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ገቢው ከየሚመ ለከታቸው ላይ ክትትል ተደርጎ እንዲሰበሰብ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም መሰብሰቡን የሚገልጽ ማስረጃ በግብረ መልስ ያልተገለፀ ስለሆነ ያልተሰበሰበ የንግድ ስራ ትርፍ ግብር በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

**ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች**

32. ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ62 መ/ቤቶች ብር 18,155,823.39 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡የገቢ ደረሰኞችን ለኦዲት ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከል ከብር 500,000.00 በላይ ከፍተኛውን የሚይዙት፡-

ደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ገን/ኢኮ/ትብብር ጽ/ቤት ብር 3,627,347.75 የያዙ ብዛት 44 ጥራዝ፤አንከሻ ጓጉሳ ወረዳ ብር 2,386,251.03 የያዙ፣ ፎገራ ወረዳ ብር 1,170,345.00 የያዙ፣ ተሁለደሬ ወረዳ ብር 997,447.00 የያዙ፣መተማ ወረዳ ብር 980,395.74 የያዙ፣አንዳቤት ወረዳ ብር 666,690.53 የያዙ፣እናርጅ እናውጋ ወረዳ ብር 659,810.00 የያዙ፣ወንበርማ ወረዳ ብር 619,615.00 የያዙ፣ሲያ ደብርና ዋዩ ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 574,030.00 የያዙ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ስራ አልቀረቡም፡፡

ለኦዲት ባልቀረቡት ደረሰኞች ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ባለመረጋገጡ በጉዳዩ ላይ አስተያየት ለመስጠት ገደብ የተጣለበትና ማጭበርበር ተሰርቶባቸው ይሁናል የሚል ጥርጣሬን ያሳደረ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ተፈልገው ቀርበው የገቢው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥና ደረሰኞቹን በሰወሩ/ባላቀረቡ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ በየሪፖርቶቹ ብናሳስብም ብር 405,341.53 (2.23%) የያዙ የገቢ ደረሰኞች ብቻ ለውስጥ ኦዲት ቀርበው የተረጋገጡ ስለመሆናቸው በተሰጠው የኦዲት ሪፖርት ግብረ መልስ የተገለጸ ሲሆን ለቀሪው የተወሰደው እርምጃ እስከዚህ ጥንቅር ሰኔ 23/2009 ዓ/ም ድረስ ምላሹ አልተገለፀም፡፡

**የተሰብሳቢ ሂሣብ ኦዲት ውጤት**

**በወቅቱ ያልተሰበሰበ (ያልተወገደ) ተሰብሳቢ ሂሣብ**

33. የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ117 መ/ቤቶች ብር **1,616,834,934.47** በወቅቱ የፋይናንስ አሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ/ሳይወገድ ተገኝቷል፡፡

ተሰብሳቢ ሂሳቦች የራሳቸው የተወሰነ የመሰብሰቢያ/የመወገጃ ጊዜ እንዳላቸውና በመመሪያው መሠረት ተገቢው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በቢሮው በቁጥር 6/2004 በክፍል 4 በተላለፈው መመሪያ የተገለጸ ቢሆንም አንዳንድ መ/ቤቶች ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ጊዜው በዘገየ ቁጥር ያለመሰብሰብ ዕድሉ እየሠፋ ስለሚሄድ መመሪያው በሚያዘው መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርቶቻችን ብናሳስብም ስለተወሰደው እርምጃ በተሰጠው ምላሽ ብር 88,550,706.86 (5.48%) ከኦዲት በኋላ የተሰበሰበ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን በቀሪው ላይ ስለተወሰደው እርምጃ ባለመገለጹ ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ስላለበት ደረጃ የታወቀ ሁኔታ የለም፡፡

በሌላ በኩል የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት እንዳስፈላጊነቱ በኦዲት ወቅት በሚመለከተው 3ኛ ወገን ማረጋገጫ እንዲቀርብለት የሚደረግ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ስለትክክለኛነቱ ከ3ኛ ወገን (ይሰበሰብባቸዋል ተብቶ ከተያዙ አካላት) ለማረጋገጥ ከተጠየቁት የተሰብሳቢ ሂሳቦች መካከል በ16 መ/ቤቶች ብር 70,481,952.57 የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ አልቀረበለትም፡፡

34. ከላይ ከተመለከተው ተሰብሳቢ መካከል በ3 መ/ቤቶች ብር 708,125.86 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሠነድ፣ መቼ እንደተሰጠ፣ ከማን እንደሚሰበሰብ እና ለምን እንደተሰጠ የሚሳይ ማስረጃ ሳይኖር በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ ይኸው ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች ይልማና ዴንሳ ወረዳ ብር 602,142.68፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን ብር 37,980.21 እና ሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ሰ/ማዕከል ብር 68,002.97 ናቸው፡፡

በመሆኑም ለሂሳቡ ትክክለኛ ዝርዝር ደጋፊ ማስረጃ ካለ እንዲያያዝና በየባለዕዳዎቹ ስም ተለይቶ

እንዲያዝና ክትትል ተደርጐ እንዲሰበሰብ/ በመመሪያው መሰረት ከመዝገብ እንዲሰረዝ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ሆኖም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚገልጽ ምላሽ አልደረሰም፡፡

35. በተጨማሪም በ51 መ/ቤቶች ብር 295,927,726.30 የመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓትን በመተላለፍ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለትን ተሰብሳቢ ሂሣብ በተመለከተ ገንዘቡ ከማን እንደሚፈለግ በባለቤቱ ስም ተለይቶ በሚያሳይ መልኩ የተመዘገበ ባለመሆኑና በጥቅሉ ስለተመዘገበ ባለቤቱን አውቆ ከሚመለከተው ላይ ለመሰብሰብ/ለማስወገድ የማያስችል በመሆኑ የተሻሻለውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በመከተል በየስሙ የተቀፅላ ሌጀር ሊዘጋጅለትና ክትትል እየተደረገ ሊሰበሰብ/ሊወገድ/ እንደሚገባው በሪፖርታችን ብናሳስብም ከዚህ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ ብር 70,559.93 ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ የተሰጠ ግብረ መልስ ባለመኖሩ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አልታወቀም፡፡

## ☐ወጪ ሒሣብ ኦዲት ውጤት፤

### የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀመበት የወጪ ሂሳብ እና ዘዴዎች

36. በበጀት ዓመቱ ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች መካከል በ15 መ/ቤቶች ብር 845,755.30 የተለያዩ የማጭበርበር ድርጊቶች ተፈፅሞበት ተገኝቷል፡፡የማጭበርበር ድርጊት የተፈፀ መባቸው መ/ቤቶችና ዘዴዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ሜጫ ወረዳ ጤና ጥበቃ እና ግብርና ጽ/ቤት ብር** 311,572.00፣ ከተለያዩ ሴክተር ጽ/ቤቶች በተለያየ ጊዜና ቦታ ስልጠና ሳይሰጥ እንደተሰጠ በማስመሰል፤በለቀቁ ሰራተኞች ስም ወጪ አድርጎ በመክፈልና ከቦታው ታሪፍ ውጭ የስልጠና አበል በመክፈል ለግል ጥቅም የዋለ ፣
- **ጓንጓ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 186,976.10 በውሉ መሠረት አገልግሎት ሳይገኝ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ፣
- **ጎንጅ ቆለላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 101,341.89 ሰራተኞች ቢሮ ውስጥ በስራ ገበታቸው እያሉ መስክ ሳይወጣ እና በተመሳሳይ ቀናት በድጋሜ፣እንዲሁም ስልጠና ሳይሰጥ ስልጠና ተሰጥቷል በሚል ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **አዲአርቃይ ወረዳ ፍርድ ቤት ብር** 63,021.44 ሰራተኞች ቢሮ ውስጥ በስራ ገበታቸው እያሉ መስክ ሳይወጣ፣ ስልጠና ከተሰጠበት ከተማ የውሎ አበል ታሪፍ በላይ የተፈፀመ፣ ለማይመለከተው ባለሙያ የተከፈለ ውሎ አበል፣ከመመሪያ ውጭ የተፈፀመ የትርፍ ስዓት ክፍያ፣

ለማይመለከታቸው ሰራተኞች የደንብ ልብስ መስጠት፤

- **ወገራ ወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ብር** 54,054.75 ለስልጠና እና ለመስክ ስራ ሳይወጣ አላግባብ ተከፍሎ የተገኘ፣ ቅዳሜና እሁድ እንዲሁም በትርፍ ስዓት ለተሰራ ስራ የውሎ አበል/የስልጠና አበል እንዲከፈል የሚደነግግ መመሪያ በሌለበት የተከፈለ እና ተግባሩ ከሙያቸው ጋር የማይገናኝ ሆኖ እያለ መስክ ለወጡባቸው በሚል አላግባብ ተከፍሎ ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **ግሸራቤል ወረዳ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ብር** 39,585.19 በግራር አምባ ቀበሌ የምንጭ ግንባታ ሥራ ሲከናወን የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን ግንባታው ሳይሠራ እንደተሠራ በማስመሰል አላግባብ የተከፈለ፣
- **ፎገራ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽ/ቤት ብር** 26,669.24 በሌሉና በፅ/ቤቱ በማይታወቁ ግለሰቦች ስም በተጭበረበረ መንገድ የተከፈለ፣ በድጋሚ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል እና በለቀቁ መምህራን ስም ተከፍሎ የተገኘ ደመወዝ፤
- **አማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር** 19,707.48፤ አላግባብ ለግል ጥቅም የዋለ ነዳጅና ግዥ ሳይፈፀም ሃሰተኛ ሰነድ ተዘጋጅቶ ክፍያ የተፈፀመበት የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት፣
- **አነደድ ወረዳ ዳገት ት/ቤት ብር** 18,272.00 የተለያዩ እቃዎች ሲገዙ ከተከፈለው ክፍያ መጠን ፊት ለፊት ቁጥር በመጨመር፣ በባዶ የወጭ ማስመስከሪያ ላይ አርሶ አደሮችን በማስፈረም ያልተቀበሉትን ገንዘብ አለአግባብ በብልጫ በማጽደቅ ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **መተማ ወረዳ ኮኪት 1ኛ/ደ/ት/ቤት** 12,110.00፦ በራሪው/ኦርጅናል/ ደረሰኝ ሂያጅና ቀረ በማበላለጥ፤የጽ/መሳሪያ ግዥ፤ለንብረት ማጓጓዣ እና ከደመወዝ በላይ ያልተፈቀደ ክፍያ፤ ለትምህርት ጥራት ሽልማት በሚል አላግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **እንፍራንዝ ከተማ ንዑስ መዘጋጃ ቤት ብር** 6,700.00 **ለስራ** ከተለያየ ተቋም በድጋሜ የተከፈለ እና ለግል ጥቅም የዋለ የውሎ አበል እና ትራንስፖርት ወጭ፣
- **ደቡብ አቸፈር ወረዳ ውሃ ሀብት ልማት ጽ/ቤት ብር** 4,415.21 ለምንጭ ማጎልበት ስራ በሚል በባለሙያ የተለያዩ የውሃ ግንባታ ዕቃዎች ወጪ ሆኖ ለምንጭ ማጎልበት ስራ ሳይውል ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **ይስማላ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ብር** 1,330.00 የጤና አጠባበቅ ጣቢያው መፀዳጃ ቤት የጥገና ስራ ሳይከናወን ሃሰተኛ ማስረጃ ቀርቦ ለግል ጥቅም የዋለ ሂሳብ ይገኙበታል።

በመሆኑም ድርጊቱን ከፈጸሙት ኃላፊዎች እና ሰራተኛዎች የሚፈለገው የህዝብ ሀብት ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 90,954.81(10.75%) የተመለሰና ብር 282,327.17(33.38%) በፍታብሔርና በወንጀል ክስ ሂደት ላይ

ያለ መሆኑን በሪፖርት ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ አልታወቀም፡፡

**ለሚመለከተዉ ፈሠስ ሳይደረግ የቀረ የተጨማሪ እሴት ታክስ**

37. በ33 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,281,536.42 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ ገንዘቡ በወቅቱ ፈሠስ መደረጉን ክትትል ባለመደረጉ ታክሱ ከመንግስት ተቋማት ተሰብስቦ ለረዥም ጊዜ በታክሱ ሰብሳቢዎቹ እጅ እየተያዘ ለስራ ማስኬጃ የሚውልበትና ከጊዜ ብዛትም ፈሰስ የማይደረግበት ሁኔታ በመኖሩ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለግብር አስገቢው መ/ቤት ፈሰስ መደረጉ እንዲረጋገጥ ሆኖ ለወደፊቱም በክልል ደረጃ የተጀመረው የመንግስት ተቋማት ታክስን ቀንሶ የማስቀረት አሠራር እስከ ታችኛው አደረጃጀት ድረስ እንዲወርድ በሪፖርታችን ብናሳስብም የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ምላሽ አልደረሰንም፡፡

**አላግባብ የተፈጸመ ክፍያ፤**

38. ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀሙ ስለመሆናቸው ሲጣራ በ114 (51.58%) መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈፀም በብልጫ እንዲሁም የመስክ ስራ ላላከናወኑ ሠራተኞች የተከፈለ የውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች በድምሩ ብር 43,200,227.99 አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተከፈለው ክፍያ ከብር 300,000.00 በላይ ድርሻ ከሚይዙት መ/ቤቶች መካከል፡-

- **ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ብር 19,791,788.63** ለሁለገብ ስታዲዮም ግንባት ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ውሃ መስኖና ኢነርጅ ልማት ቢሮ ብር 7,867,575.09** ቢሮው ላከናወነው የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ክፍያ ሲፈፀም ግንባታውን ላላከናወነ ድርጅት የተከፈለ ክፍያ፣
- **ቦረና ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 1,549,670.78** በመደበኛ ስራ ቦታ ላይ አላግባብ የተከፈለ ውሎ አበል፣ከወረዳው በጀት ላይ አላግባብ ለጤና መድህን ድርጅት የተለያዩ ህትመቶች የተከፈለ፣ ለጤና ጣቢያ ግንባታ የጨረታ 1ኛው አሸናፊ እያለ ባልታወቀ ምክንያት 2ኛው እንዲያሸንፍ በመደረጉ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ ግዥ፣
- **አማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ብር 997,866.75** የተለያዩ መሳሪያዎችንና የመሳሪያ አካላትን ግዥ በማከናወን ክፍያ ተፈጽሞ ሳለ መሳሪያዎቹ ያልቀረቡለት፤
- **ጃማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 978,141.68** ለተለያዩ ሰራተኞች በስራ ገበታቸው ላይ እያሉ የተከፈለ የውሎ አበል፣ለአስተዳደር ጽ/ቤት የህንፃ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ከውለታው በላይ

በብልጫ የተከፈለ፣

- **ንግድ፣ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ ብር** 908,910.30 ለሰሊጥ መጋዘን ግንባት ክፍያ ሲፈጸም በብልጫ የተከፈለ፣በመደበኛ የስራ ቦታ ለተሳተፉ ሰራተኞች አላግባብ የተከፈለ የስልጠና አበል፣የኢንዱስትሪ ሽድ ግንባታ ለተከናወነበት በጎንደር፣በደብረ ብርሃን እና ባህር ዳር ከተሞች ክፍያ ሲፈፀም ላልተሰራ ስራ የተከፈለ፣
- **ይልማና ዴንሳ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 807,726.98 በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገዶች ተደራሽነት ፕሮግራም ለስራ ተቋራጭ ከተያዘው ውል በላይ አላግባብ በብልጫ የተከፈለ፣
- **መተማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 543,329.44 የመኪና መለዋወጫ ዕቃ ግዥ ሲፈፀም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ እያለ ያለ ተጨባጭ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው አቅራቢ በመፈፀሙ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈጸመ ግዥ፣ለወረዳው ሴክተር መ/ቤቶች የሚውል የቢሮ ግንባታ ሲከናወን ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ ተከፈለ፣
- **ደብረ ማርቆስ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 488,702.23 የኮብል እስቶን መንገድ ሲሰራ ቤት ለፈረሰባቸው ግለሰቦች ክፍያ ሲፈፀም አላግባብ የተከፈለ፣ የተፋሰስ ጥገናና ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ፣ ለኮብል ስቶን ንጣፍ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **እናርጅ እናውጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 459,587.39 ለጽ/ቤት ህንጻ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 434,555.66 ለተለያዩ ሴክተር መ/ቤት ሰራተኞች ስራ ገበታቸው ላይ እያሉ፣በድጋሜ እና አላግባብ በብልጫ የተከፈለ ውሎ አበል፣ለእብናት 2ኛ/ደ/ት/ቤት መምህራን የሰኔ ወር ደመዎዝ ሲከፈል በብልጫ የፀደቀ እና በተለያዩ ቀበሌዎች ለሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ ተፈፀመ፣
- **ጤና ጥበቃ ቢሮ /MDG/ ብር** 419,669.22 የቢቡኝ ወረዳ ለሚያስገነባው የሆስፒታል ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ደብረ ብርሀን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር** 357,752.44 የላፒደሪ ወርክ ሾፕ ግንባታ ሲከናወን ከውል በላይ አላግባብ የተፈጸመ ክፍያ፣
- **ስከላ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 354,254.92 ለተለያዩ ሴክተር መ/ቤት ሰራተኞች የውሎ አበል ሲፈፀም በድጋሜ እና በብልጫ፣ለጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ፣ ለት/ቤቶች የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም በብልጫ የተከፈለ፣
- **ማቻከል ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 349,741.81፤ ለግንባታ ሲከናወን የተሰጠው ቅድመ ክፍያ በተቋራጩ ስም ሳይሆን በግዥ ኦፊሰር ስም የተያዘ፣ ለተለያዩ የጤና ዘመቻ ስራ ሳይሰራ

እንደተሰራ ተደርጎ የተከፈለ ውሎ አበል፣

- **ዳዋ ጨፋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 349,492.21 ለተለያዩ ሰራተኞቸ በድጋሜ የተከፈለ የውሎ አበል፣
- **አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 344,274.00 ለተለያዩ ሰራተኞች በስራ ገበታቸው ላይ እያሉ የተከፈለ የውሎ አበል፣ለቀበሌ የልማታዊ ሴፍቲኔት ማህበረሰብ ተጠቃሚዎች ፕሮግራም የወር ደመወዝ ሲከፈል በብልጫ የተከፈለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የ2008 በጀት ዓመት አላግባብ የተከፈለ ክፍያ ከ2007 በጀት ዓመት ብር 13,917,929.12 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ39 ሲቀንስ በገንዘብ መጠን ግን በብር 29,282,298.87 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ አላግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 360,501.46(0.83%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ገንዘብ ስለመተካቱ እስከ ሰኔ 23/2009 ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡ ይህም በተለያዩ መንገዶች አላግባብ ክፍያዎችን መፈጸም ካለፈው ዓመት እየተባባሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

## የግንባታ ስራዎች ወጪን በተመለከተ፤

39. ማንኛውም የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት በባለሙያ እየተረጋገጠ መፈጸም ሲገባው የግንባታ ክፍያ አፈፃፀም መመሪያን ባልተከተለ መንገድ በ38 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,926,633.99 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ከዚህም ውስጥ ከብር 300,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-
    - **ፍኖተ ሰላም ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 9,414,905.39፣ለኮብል ስቶን መንገድ ግንባታ ጠረጋ ስራ ላከናወነው ተቋራጭ ክፍያ ሲፈፀም፤
    - **ቻግኒ ከተማ አስ/ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 6,224,530.43፤ በከተማ አገልግሎቱ ዲሽቦይ፣ አጥር፣ሽድ፣ቁራ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም፣
    - **ጭልጋ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 4,674,382.08፤ በወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት የት/ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም የሌላ ግንባታ ፕሮጀክት የስራ ልኬት ወረቀት ቀርቦ ክፍያ የተፈፀመ፣
    - **ጓንጓ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,986,397.58፤ የመስኖ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም፣
    - **ደባርቅ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,768,490.89፤ የት/ቤት እና የውሃ ጉድጓድ ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም ፣
    - **ፋግታ ለኮማ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 868,940.20 ለት/ቤት ግንባታ ክፍያ ሲፈፀም፣
    - **ደጀን ወረዳነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 479,656.63 የወረዳው አስተዳደር ጽ/ቤት የቢሮ ግንባታ ክፍያ ሲፈጸም፣

- **እብናት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 335,335.73፤ የት/ቤት የመፀዳጃ ቤት ግንባታ እና የቢሮ ግንባታ ለተሰራበት ክፍያ ሲፈጸም፣
- **ሊቦ ከምከም ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 379,836.98፤ በውሃ ጽ/ቤት በተለያዩ ቀበሌዎች ለተገነቡ የንጹህ ውሃ መጠጥ ተቋማት ክፍያ ሲፈፀም፣
- **ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር** 463,659.58 የት/ቤት የመፀዳጃ ቤት ግንባታ ፣የምንጭ ማጎልበት ግንባት፤ለጤና ኬላ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፤የእጅ ጉድጓድ ግንባታ እና የምንጭ ማሰባሰቢያ ገንዳ ግንባታ፤

ስራው ስለመከናወኑ የሚያሳዩ የስራ ልኬት ወረቀት /የክፍያ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት/ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈፃሞ የተገኘባቸው ሲሆኑ ሥራው በትክክል ስለመሠራቱ በገለልተኛ የምህንድስና ባለሙያ እንዲረጋገጥ ሆኖ ያልተሰራ መሆኑ ከተረጋገጠ ገንዘቡ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ እና ድርጊቱን በፈጸሙት ባለሙያዎች ላይ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባዉ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ የግንባታ ማስረጃ ሳይቀርብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ ብር 29,292.80 (0.09%) የተተካ ሲሆን ቀሪው ሂሳብ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ይህ ጥንቅር እስከተሠራበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ ለመ/ቤታችን አልተገለጸም፡፡

**ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ**

40. ማንኛውም □አ□ ተ□□ሞ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተቋቢ□ ማስረጽ መቅረቡ መረ□ቶዓ ሲቶባ ይህን በመተላለፍ በ63 መ/ቤቶች የተለያየ የዕቃና አገልግሎት ግዥ ሲፈጸም ለተከፈለው ብር **55,161,544.30** የወጪ ደረሰኝ/ፋክቱር ሳይቀርብለት □አ□ ተ□□ሞና በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ ማስረጃ ያልቀረበለት ወጪ ካለፈው ዓመት ብር **24,831,883.94** ጋር ሲነፃፀር በ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች በቁጥር 24 የቀነሰ ሲሆን በገንዘብ መጠን ግን በብር 30,329,660.39 ጨምሮ ተገኝቷል፡፡ ይህም በማስረጃ አቀራረብ ዙሪያ ያለው ችግር እየተባባሰ መሄዱን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ባለበጀት መ/ቤቶች በከፈሉት ገንዘብ ልክ ተገቢውን ዕቃ /አገልግሎት ማግኘታቸውን የሚያመለክት ለእያንዳንዱ ክፍያ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ እንዲያያዝ/ ያለማስረጃ የተከፈለው ገንዘብ ከሚመለከተው ላይ ተመላሽ እንዲሆን ለየመ/ቤቶች በፃፍነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

**ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ የወጪ ማስረጃዎች፤**

41. ክፍያዎች በተገቢው ማስረጃ ተደግፈውና መ/ቤቱ ለተጠቀመበት ዕቃና አገልግሎት በትክክል ስለመዋላቸው በኦዲት ለማረጋገጥ ክፍያ የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት

እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ32 (11.94%) መ/ቤቶች ብር 124,765,448.91 የያዙት የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 5,631,573.64(4.51%) ከኦዲት በኋላ ማስረጃ ቀርቦ በውስጥ ኦዲተር የተረጋገጠ መሆኑ በግብረ ተገልጿ። ከፍተኛ ወጪ ይዘው መረጃ ካላቀረቡት መ/ቤቶች መካከልም ከብር 300,000.00 በላይ የያዙ መ/ቤቶች፡-

- አርጡማ ፉርሲ ወረዳ ብር 97,081,534.73፣ ባቲ ከተማ ብር 6,945,873.72፣ቃሉ ወረዳ ብር 4,646,264.09፣ ሞረትና ጅሩ ወረዳ ብር 2,563,760.50፣ ተንታ ወረዳ ብር 2,318,469.17፣ ዝቋላ ወረዳ ብር 1,758,549.13፣ባህር ዳር ዙሪያ ወረዳ ብር 1,670,553.97፣ጣቁሳ ወረዳ ብር 1,616,277.03፣ ዋግኽምራ ብሄረሰብ አስተዳደር ብር 1,299,775.54፣ጉባላፍቶ ወረዳ ብር 1,177,709.20፣ ዳዋ ጨፋ ወረዳ ብር 817,577.89፣ መቄት ወረዳ ብር 481,607.85፣ ቀወት ወረዳ ብር 429,128.15 እና ሳህላ ሰየምት ወረዳ ነ/ፋ/ድ/ስ/ማዕከል ብር 396,353.56፣

ማስረጃዎቹ ምን እንደተፈፀመባቸውና ለማጭበርበር ድርጊት አለመዋላቸው ባለመረጋገጡ ስጋት ያስከተለ በመሆኑ ቀርበው የወጪው ትክክለኛነት በውስጥ ኦዲተሮች እንዲረጋገጥ ከማድረግ በተጨማሪ ሰነዶቹን የሰወሩ/ማቅረብ የነበረባቸው ሠራተኞች ተጠያቂ እንዲሆኑ በኦዲት ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡ይሁንና ስለተወሰደው እርምጃ ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀቀበት ሰኔ 23/2009 ድረስ የሚያሳይ ምላሽ ባለመምጣቱ ግኝቱ ያለበትን ሁኔታ ማወቅ አልተቻለም።

**የግዥ ሥርዓትን ያልተከተለ የወጪ ሒሳብ**

42. ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ አፈፃፀም በስራ ላይ ባለው ዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያ መሠረት ስለመፈፀሙ እንዲሁም የተሻለ የዕቃ ጥራትና ዋጋ ለመገኘቱና የግዥ አፈፃፀም ሂደቶች ተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ151 (68.32%) ብር 85,767,773.50 ዋጋ ያላቸው ግዥዎች የግዥ ሥርዓት የሚጠይቀውን መሥፈርት ሣያሟሉ ተከናውነው ተገኝተዋል። የግዥ አፈጻፀም ችግሮች ጎልቶ የሚታይባቸው ከብር 1,500,000.00 በላይ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት መ/ቤቶች፡-

- **ቻግኒ ከተማ አስ/ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 9,719,123.08**፤የኮብል እስቶን ንጣፍ ስራ፣የዲች ግንባታ፣የኮብል እስቶን ድንጋይ ግዥ ሲፈፀም ያልግልጽ ጨረታ የተከናወነ እና የግዥ ሰራተኞች ሳያውቁት በአመራሮች ትዕዛዝ የተፈጸመ ፣ለከንቲባ ጽ/ቤት የሚውል የመኪና ጎማና የመኪና ጌጣጌጦች፣የተለያዩ የአትክልት ዘር ግዥ ሲፈፀም፤
- **ሰቆጣ ከተማ አስ/ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር 7,202,367.23**፤ የግንባታ ቁሳቁስ ግዥ ሲፈፀም ንግድ ፈቃድ ከሌለው አቅራቢ የተፈፀመ፣የቫት ተመዝጋቢ ካልሆነ ድርጅት የተፈፀመ፤ የኮብል እስቶን

ምንጣፍ ግንባታ መመሪያ ከተፈቀደው ውጭ ለጥቃቅንና አነስተኛ ለተደራጁ ተቋማት፤ ከግዥ ጣሪያ በላይ በቀጥታ የተፈፀመ ግዥ፤

- **ሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳር ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 5,612,897.48፤ሁለገብ የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ የታፔላ ስራ ሲከናወን፤
- **ቴክኒክና ሙያ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ /MDG/ ብር** 3,120,542.26 በከለላ ወረዳ ላስገነባው የጀኔራል መካኒካል ወርክ ሾፕ ህንጻ ግንባታ፣ለተለያዩ ቴክንክና ሙያ ተቋማት አገልግሎት የሚውል የተለያዩ የማሰልጠኛ መሳሪያዎች ግዥ ሲፈጸም፤
- **ጤና ጥበቃ ቢሮ ብር** 2,545,220.28፤ በእንጅባራ ከተማ የሆስፒታል ግንባታ፤ለጤና አጠባበቅ ጣቢያ ግንባታ፤
- **ቀወት ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 2,198,001.11 የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች፣ የኤሌክት ሮኒክስ ዕቃዎች እና ቋሚ ዕቃ ግዥ፡
- **ሜጫ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 2,182,686.53 ለሴክተር መ/ቤቶች የተለያዩ የጽ/መሳሪያዎች፣አላቂ እቃዎች፣የግንባታ ቁሳቁሶች ግዥ ሲፈፀም፣ለተለያዩ የወረዳው ቀበሌዎች የመንገድ ስራ ለማሰራት የግንባታ መሳሪያ ኪራይ ሲፈፀም፤
- **ሲያ ደብርና ዋዩ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 2,162,900.63፤ የመኪና መለዋወጫ ዕቃ፣የውሃ ዕቃዎች፣የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ ግዥና ጥገና፣ የአላቂ የቢሮ ዕቃ፣የእንስሳት ህክምና የግንባታ ዕቃዎች፣ለትምህርት ማጠናከሪያ ቁሳቁስ ግዥ፣የመምህራን እስታፍ ቢሮ ግንባታ፣ የውሃ ጉድጓድ ግንባታ ግዥ፤ የተሽከርካሪ ጥገና ሲከናወን፤
- **ኤፍራታና ግድም ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,662,962.48 ለሴክተር መ/ቤቶች የሚውል ኮምፒውተር፣ኤሌክትሮኒክስ፣የመኪና ጎማ እና ቋሚ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፅም፣
- **ሚዳና ወረሞ ወረዳ ነ/ፋድ/ስ/ማዕከል ብር** 1,642,815.41፤ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ግዥ ሲፈፀም እና ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ አቅራቢ እያለ መሰረታዊ ባልሆነ ምክንያት ከጨረታ ውድድር ውጭ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ባልሆነ መንገድ የተፈፀመ፤
- **ደብረ ብርሀን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ብር** 1,547,261.30፤ የተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ሲፈፀም፤

  የተለያዩ የግዥ ህጉን ያልጠበቁ አፈጻጸሞችን በመከተል (ያለግልጽ ጨረታ፤ያልግዥ ጥያቄና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት የተገኘ) የተከናወነ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ግኝቱ ሊከሰት የቻለውም የግዥ መመሪያው በተገቢው መንገድ በሥራ ላይ ካለማዋል የተነሣ ገንዘቡ ተገቢዉን ዕቃ (አገልግሎት)ሳያስገኝ እና ፍትሃዊ ውድድርን ሳያስተናግድ ግዥ እየተፈፀመ እንደሆነ በማስገንዘብ ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው

በኦዲት ሪፖርቶች አሣስበናል፡፡

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረገዉ የግኝ ሂሳብ ከ2007 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝት ብር 126,923,643.06 ጋር ሲነፃፀር በመ/ቤት ቁጥር በ15 እና በገንዘብ መጠን በብር 41,155,869.56 ቀንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የግኝ መመሪያውን በመከተል በኩል መጠነኛ መሻሻል መኖሩን ያመላክታል፡፡

**የተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ፤**

**ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀለት ተከፋይ ሂሳብ፣**

43. የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ43 መ/ቤቶች ብር **174,313,617.20** በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቼ እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ በግብረ መልስ እንደተረጋገጠው ብር 476,000.00 ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የተዘጋጀለት መሆኑ በግብረ መልስ የተገለፀ ሲሆን ቀሪው ብር 173,837,617.20 ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰኔ 23/2009 ዓ.ም ድረስ የተወሰደውን እርምጃ የሚያሳይ ግብረ መልስ ባለመኖሩ ለምን ያህሉ ገንዘብ ተቀጽላ ሌጀር እንደተዘጋጀ ማወቅ አልተቻለም፡፡

**የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ኦዲት ውጤት**

44. የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች በክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 178/2003 አንቀጽ 53 እና በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 02/2003 እና ተያያዥ የህግ ማዕቀፎች አግባብ ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው፤ ክትትል እየተደረገባቸውና በየዓመቱ ቆጠራ እየተከናወነ የንብረት ሒሳቡም በመ/ቤታችን ኦዲት መደረግ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በበጀት ዓመቱ በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 221 መ/ቤቶች መካከል በ82(37%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም የተጠቀሱትን የንብረት አስተዳደር ግድፈቶች በማረም ሊከሰት የሚችለውን ከፍተኛ የመንግስት ሃብት ብክነት እንዳይከሰት ተገቢው የንብረት አስተዳደር፤ አያያዝና አጠቃቀም በየመ/ቤቱ እንዲጠናከር በየሪፖርቶቻችን አሳስበናል፡፡

**የንብረት ሂሳብ ጉድለት፤**

45. የ2008 በጀት ዓመት ሒሣባቸው ኦዲት ከተደረገ መ/ቤቶች በድምሩ ብር **989,293.77** ጉድለትና ማጭበርበር የተገኘ ሲሆን ጉድለት/ማጭበርበር የተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር፡-

- **መተማ አብርሃ ጅራ ሁር ኡመር መንገድ ስራ ፕሮጀክት ብር 278,237.38**፤ የፕሮገክቱ ንብረት

ክፍል ሰራተኛ ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣

- **አንዳሳ ደሮ ብዛት ማዕከል ብር** 253,635.27፤የንብረት ክፍል ሰራተኛ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- **ቆቦ ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት ብር** 189,662.06 የንብረት ክፍል ሰራተኛው ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣
- **ኮምቦልቻ ደሮ ብዛት ማዕከል ብር** 96,849.76 የንብረት ክፍል ሰራተኛው ያንቀሳቀሱት የንብረት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ ጉድለት፣
- **ምዕራብ በለሳ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት** 85,164.63 በንብረት ወጭ ደረሰኝ /ሞዴል 22/ ወጪ ተደርገው ለጠያቂው ያልተሰጡ/በጠያቂው ያልተወሰዱ/ንብረቶች እንደተወሰዱ ለማስመሰል አሃዝ ደልዞ በመቀየር፤ባልተፃፈበት መስመር ላይ ተጨማሪ ንብረት እንደወጣ በመፃፍ በተጠቃሚው ያልተወሰዱ ንብረቶችን እንደወሰዱ በማስመሰል ለግል ጥቅም የዋለ፣
- **ክልል ምክር ቤት ብር** 49,772.30፤ የንብረት ክፍል ሰራተኛዋ ያንቀሳቀሱት ሂሳብ ተመዛዝኖ የተገኘ የንብረት ጉድለት፣
- **አዊ ብሄረሰብ ዞን ጤና መምሪያ**፤ የክሊኒካል ነርስ ባለሙያው ከዞኑ ጤና ጥበቃ መምሪያው የብር 35,972.37 መድሃኒቶችና ዋጋቸው የማይታወቁ ብዛት 643 የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎችን ወጪ አድርገው ከወሰዱ በኋላ በወቅቱ ይሰሩበት ለነበረዉ ለጃዊ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ገቢ ሳያደርጉ ለግል ጥቅም የዋለ፣

በመሆኑም ከንብረት ሰራተኞች የሚፈለገው ጉድለት ላይ ተገቢውን ክትትል በማድረግ ማስተካትና አጥፊዎች በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው ባሳሰብነው መሰረት ብር 170,909.30 (18.90%) በፍታብሔርና በወንጀል ክስ እንዲሁም ማስረጃ በማሰባሰብ ሂደት ላይ መሆኑ ከፍትህ አካላት የተገለፀልን ሲሆን ውሳኔው እየተጠበቀ ይገኛል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**የማጠቃለያና የማሻሻያ አስተያየቶችን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡**

**በኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታና የኦዲት ሽፋንን በተመለከተ**

46. በ2009 በጀት አመት በኦዲት ልማት ሰራዊት ግንባታ ረገድ ከፍተኛ ርብርብ የተደረገ መሆኑና በቀጣይ ጊዚያት ሙሉ የሰራዊት አቅም ላይ የደረሰ ፈፃሚ ሃይል እንዲፈጠር ምቹ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ይህም ከዓመቱ እቅድ አንጻር 93% ከኦዲት ሽፋን በመ/ቤት ቁጥር አንፃር ከ60% እና ከበጀት ከ86% በላይ አፈፃፀም መኖሩ አበረታች ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲት አፈፃፀም በአማካይ ከ91% በላይ ቢሆንም በአዲስ አደረጃጀት መዋቀሩ አበረታች ሆኖ በአጠቃላይ የኦዲት ሽፋን ለማሳደግ በሰፊው መስራት ይኖርብናል፡፡

**የኦዲት አስተያየትን በሚመለከት፤**

47. የ2008 በጀት ዓመት ሒሳባቸው በመደበኛነት ኦዲት ከተደረጉ 221 መ/ቤቶች ውስጥ 6 (2%) የሚሆኑ መ/ቤቶች ንጹህ የሚል አስተያየት እንዲሁም ከ203 (76)%) የሚሆኑት "**ከዚህ በስተቀር**" የሚል ኦዲት አስተያየት ያገኙና ‹‹**አስተያየት መስጠት አልተቻለም**›› እና ‹‹**አጥጋቢ አይደለም**›› የሚል የኦዲት አስተያየት ያላቸው መ/ቤቶች ብዛት ውስን መሆኑ አብዛኞቹ የክልላችን መ/ቤቶች የክልሉን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መሰረት አድረገው በጀትን ለመምራት ጥረት እያደረገ መሆኑን ያመላክታል፡፡

**ምላሽ አሰጣጥን በሚመለከት**

48. የ2009 በጀት ዓመት ሒሳባቸው ኦዲት የተደረጉ ተቋማት በምላሽ አሰጣጥ ረገድ ግፊት ያለበት ቢሆንም መሻሻል የታየበት ነው፡፡

**የጥሬ ገንዘብ ሒሳብ ኦዲትን በሚመለከት**

49. የ2009 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች የወቅቱና *የቀትም* ገንዘብ ያገሮች ላይ በድምሩ ብር **667,269.82** *በጉድለት ተገኝቷል፡፡* በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ መከታተያ ሌጀር መሠረት መገኘት ያለበት እና በካዝና ተገኝቶ የተቆጠረ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ሲነጻጸር በ15 መ/ቤት ብር **4,735,882.41** የቆጠራ ውጤት ከሌጀር ከወጪ ቀሪ በማነስ መገኘቱና 64 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ላይ ያለውን የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለባቸው ናቸው፡፡

**የገቢ ሂሣብን በተመለከተ**

50. የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረገ 5 መ/ቤቶች ብር 3,178,432.91 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም የዋለና በ69 መ/ቤቶች ብር **30,395,650.08** ሥራ ላይ ባለው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት መሠረት በወቅቱ ሳ□ሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ገቢ በትክክል መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ገቢ የተሰበሰበባቸው ደረሰኞች ለኦዲት ተሟልተው እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ62 (28%) መ/ቤቶች ብር 18,155,823.39 የያዙ የገቢ ደረሰኞች ለኦዲት ሊቀርቡ ባለመቻላቸው የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በ9 መ/ቤቶች ደግሞ ብር 2,916,894.29 የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

**ተሰብሳቢ ሂሳብን በሚመለከት**

51. የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት ከተደረጉ መ/ቤቶች ውስጥ በ117 መ/ቤቶች ብር 1,616,834,934.47 በወቅቱ በፋይናንስ የአሠራር ስርዓት መሠረት ሣይሰበሰብ (ሳይወገድ) ተገኝቷል፡፡ በ3 መ/ቤቶች ብር 708,125.86 ትክክለኛ ተሰብሳቢ ሂሳብ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ማስረጃ በሌለበት በተሰብሳቢ ሂሳብ ተይዞ መገኘቱና በ51 መ/ቤቶች ብር 295,927,726.30 የሆነ የተሰብሳቢ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

**የወጪ ሂሳብን በሚመለከት**

52. በ15 መ/ቤቶች ብር 845,755.30 የተለያዩ የማጭበርበር ዘዴዎችን በመጠቀም ለግል ጥቅም ውሎ መገኘቱ ሲሆን በ33 መ/ቤቶች ለስራ ተቋራጮች የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 6,281,536.42 በትክክል ለሚመለከተዉ ገቢ ሠብሳቢ መ/ቤት ፈሠስ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብለት ተገኝቷል፡፡ በ113 (51%)መ/ቤቶች የተለያየ ዕቃና አገልግሎት የተፈጸሙ ክፍያዎች በድምሩ ብር **43,200,227.99** አላግባብ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ የግንባታ ክፍያ በውሉና በሥራ ዝርዝሩ መሠረት መከናወኑ ሳረጋገጥ በ38(17%) መ/ቤቶች በድምሩ ብር 29,926,633.99 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣ በ63(28.50%) መ/ቤቶች የዕቃና አገልግሎት ግዥ ብር **55,161,544.30** የወጪ ደረሰኝ /ፋክቱር ሳይቀርብለት □አ□ ተ□□ሞና ተመ□□ቦ መቆኘቱ፣ ክፍያዎች የተፈጸመባቸው የወጪ ማስረጃዎች ተሟልተው ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቀው በ32 መ/ቤቶች ብር 124,765,448.91 የያዘ የክፍያ ማስረጃ ለኦዲት ሳይቀርብ ቀርቷል፡፡

**የተከፋይ ሂሳብን በሚመለከት**

53. የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች መካከል በ43 መ/ቤቶች ብር **174,313,617.20** በመንግስት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለማን እንደሚከፈልና መቸ

እንደሚከፈል የሚያሳይ የተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር ሣይዘጋጅለት ተገኝቷል፡፡

**የንብረት አያያዝ፤ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ**

54. የ2008 በጀት ዓመት ሒሣባቸው በመደበኛው ኦዲት ከተደረጉት 221 መ/ቤቶች መካከል በ82 (37%) መ/ቤቶች የንብረት ኦዲት ማድረግ ሳይቻል ሲቀር ኦዲት ከተደረጉ መቤቶች ብር 989,293.77 በጉድለትና በማጭበርበር ለግል ጥቅም ውሎ ተገኝቷል፡፡

**የተከበሩ አፈ-ጉባዔ!**

**የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት!**

**ክቡራትና ክቡራን!**

**ከዚህ ቀጥሎ የማሻሻያ አስተያየቶችን አቀርባለሁ፡፡**

በዚህ በጀት ዓመት ባቀረብነው የመ/ቤታችን ዕቅድ አፈፃጸም ላይ የተስተዋሉ ውስንነቶች፤ በኦዲት ተደራጊዎች የታዩ ግኝቶች ተሻሽለው የኦዲት ሽፋናችን እንዲያድግና የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር አመራር ሥርዓት መጠናከር እንዲችል የሚከተሉትን የማሻሻያ አስተያቶች አቀርባለሁ፡፡

**የኦዲት ሽፋንን ለማሳደግ ጥራቱን እና ውቅታዊነቱን የጠበቀ ለማድረግ ከአደረጃጀት አንጻር ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡**

55. በክልላችን ያለው ልማት እየጐለበት በመምጣቱ የኦዲት ተደራጊ ተቋማት ብዛትና በጀት እየጨመረ የሚገኝ ሲሆን የኦዲት ሽፋኑን ማሳደግና ጎን ለጎንም ጥራቱንና ወቅታዊነቱን የጠበቀ ማድረግ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለይም ማህበረሰቡ ስለ ኦዲት ሙያ ግንዛቤ እየያዘ የጥቆማ ተሳትፎው በመጨመሩ እንዲሁም ለፍትሃዊ የውሳኔ አሰጣጥ ሲባል በየደረጃው ካሉ ፍርድ ቤቶችና የስነ-ምግባርና ጸረ-ሙስና ኮሚሽን የሚቀርቡ የልዩ ኦዲት ጥያቄዎች በስፋት እየቀረቡና በተለየ ትኩረት ተይዘው ካልተሰሩ አሁን ባለው አደረጃጀት ከመደበኛው ኦዲት ስራ ጋር ደርቦ በመስራት ለጥያቄው ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት ያላስቻለና ከስራው ጥራትና ብዛት አንጻር ራሱን በተለየ አደረጃጀት መምራት አስፈላጊ አድርጎታል፡፡

ይኸውም የልዩ ኦዲት ስራ ከባህሪው ካስቸኳይነቱትና በህግ ፊት ለቀጠሮ የሚፈለግ መሆኑ፤ ከዓመት ዓመት በስፋት እየጨመረ በመምጣቱና ጊዜ የማይሰጠው ስራ በመሆኑ የመደበኛ ስራውን ሊያስቆም በሚችል ደረጃ ጫና እያስከተለ በመምጣቱ ራሱን በቻለ ዳይሬክቶሬት መምራት ይቻል ዘንድ አደረጃጀቱ ምላሽ እንዲያገኝ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

**የኦዲት ግኝቶች እርምጃ አወሳሰድና የፋይናንስ ተጠያቂነትን ስለማጠናከር፤**

56. ኦዲት ተደራጊዎች በምላሽ አሰጣጣቸው እየወሰዱት ያለው እርምጃ አዝጋሚና ተጨባጭ ለውጥ የሚያመጣ ሆኖ ባለመገኘቱ መልስ በማይሰጡና እርምጃ በማይወስዱ፤ በኦዲት አገልግሎቱ እየተጠቀሙ ከዓመት ዓመት በማይሻሻሉ ኦዲት ተደራጊዎች ላይ በየደረጃው የሚገኙ በምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎችና በፍትህ አካላት አማካኝነት እንዲሁም የኦዲት እርምጃ አወሳሰድ ክትትልና ድጋፍ ግብረ ኃይል በየደረጃው በማቋቋምና በማጠናከር የግልጽነትና ተጠያቂነት ስርዓቱ ሊጠናከር ይገባል፡፡

ይህን ክትትልና ተጠያቂነት ለማጠናከር በመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዩች ቋሚ ኮሜቴ (Public Accounts Committee) በክልሉ ምክር ቤት መቋቋም ይችል ዘንድ ከፌደራልና ከሌሎች አቻ ክልሎች የተወሰደው ልምድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

**የጥሬ ገንዘብና የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የሚታየውን ችግር ስለመቅረፍ**

በአብዛኞቹ መ/ቤቶች የጥሬ ገንዘብን ሂሳብም ሆነ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ ተቋቁሞ የማይሠራባቸውና በየጊዜው ቆጠራ የማይከናወን በመሆኑ የጥሬ ገንዘብንና የንብረት አያያዝና አጠባበቅን በኦዲት አረጋግጦ ጉድለት መኖር አለመኖሩን አስተያየት መስጠት እንዳይቻል እያደረጉ ስለሚገኙ የመ/ቤቶች ስራ አመራሮችና ፈጻሚዎች በወጡ ህግጋት መሠረት የጥሬ ገንዘብንም ሆነ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ሌጀሮች በማቋቋምና በየጊዜው ቆጠራ እያከናወኑ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪው ጋር እያመሳከሩ ልዩነት ሲፈጠርም ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ተገቢው ትኩረት ሊያደርጉና ሊተገብሩ ይገባል፡፡ ይህን አለመፈጸም በራሱ በህግ ሊያስጠይቅ ይገባል፡፡

በመጨረሻም የተከበራችሁ የምክር ቤት አባላት፣ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤዎች፣ የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴና ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የፍትህ አካላትና ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሥራ ሂደት ላደረጋችሁልን የስራ ትብብር እና የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ በዚህ ሪፖርት ለተገኙት ውጤቶች ላሳያችሁት ታታሪነትና የሙያ ስነ-ምግባር ከፍተኛ ምስጋና እያቀረብኩ ሪፖርቴን በዚሁ አጠቃልላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!!

ስመኝ ካሴ እንደሻው

ምክትል ዋና ኦዲተር

ሐምሌ /2009 ዓ.ም

<u>ባህር ዳር!</u>